# ደንብ

## ሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

ተዛማጅ ሰነዶች፡- IED፣ IKA፣ IKA-RA፣ IOA፣ IOA-RA፣ ISB-RA፣ JNA፣ JNA-RA፣ JOA-RA
ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት: Chief of School Support and Well-being; Chief of Strategic Initiatives

# የክፍል አማካይ ውጤት (GPAs) እና የክፍል አማካይ ድምር ውጤት (WGPAs)

I. **ዓላማ**

የክፍል አማካይ ውጤት እና የክፍል አማካይ ድምር ውጤት ለመወሰን እና መረጃውን እንደ መግቢያ መስፈርት ለሚፈልጉ ቀጣሪዎች እና ከድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ለሥራ ቀጣሪዎች ሪፖርት ለማድረግ አመቺ የሚሆን አሠራር ለመፍጠር ነው።

II. **ትርጉም**

A. የላቀ ደረጃ ኮርሶች ማለት በከፍተኛ የትምህርት ውጤት ላይ ተመስርቶ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚሰጡ ኮርሶች ናቸው። በተመሳሳይ ደረጃ የሚመጣጠን የከፍተኛ ችሎታ (honors-level) ኮርሶች የሉም። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚሰጡ የላቀ ደረጃ ኮርሶች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የኮርስ መጽሔት እና የላቀ ምደባ እና አለምአቀፍ የባካሎሬት ኮርሶች ላይ ይካተታል።

B. ክሬዲትማለት የተጠናቀቀ ትምህርት ሚዛን ነው።

C. የክፍል ውጤት በሚከተለው መስፈርት መሰረት ክሬዲት-ለሚያስገኙ ኮርሶች በአሃዝ የሚገለጹ የተማሪው ውጤቶች ናቸው።

A = 4
B = 3
C = 2
D = 1
E = 0

D. የአማካይ የክፍል ውጤት/GPA ማለት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶች የተገኘ አማካይ የክፍል ውጤት ነጥብ ነው። ሰክሽን III.A. ላይ እንደተገለጸው ኮርሶች በአጠቃላይ የክፍል ውጤት አማካይ/GPA ስሌት ውስጥ የተካተቱ ሲሆን በተማሪው(ዋ) ትራንስክሪፕት ላይ ሪፖርት ይደረጋል። አማካይ የክፍል ውጤት/GPA የሚሰላው በስሌቱ ውስጥ ከተካተቱት የኮርስ ክሬዲቶች የተገኘውን አጠቃላይ የነጥብ ብዛት ኮርሶቹ ለሚያስገኙት ውጤት በማካፈል ነው። ከነጥብ በኋላ ያለው ሦስተኛው አሃዝ ከአራት የሚበልጥ ከሆነ አማካይ የክፍል ውጤቱ/GPA ሁለተኛው የዴሲማል ነጥብ ቀጥሎ ወዳለው የዴሲማል ቁጥር ይጠጋጋል።

E. የላቀ ችሎታ ኮርሶችተመሣሣይ ይዘት ያላቸውን የልቀት ያልሆኑ ኮርሶች ያካትታሉ የሆነ ሆኖ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ኮርሶች ረቂቅ እና ከፍተኛ የአስተሳሰብ ችሎታን መጠቀም ይፈልጋሉ።እንዲሁም ምርምር እና የበለጠ ጠንካራ ፕሮጀክቶችን ይሠራሉ። የላቀ ደረጃ ኮርሶች (Honors courses) በሞንትጎመሪ ካውንቲ

ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ መጽሔት/High School Course Bulletinላይ ተዘርዝረዋል።

F. ትራንስክሪፕት የመጨረሻ ውጤት እና በእያንዳንዱ ኮርስ የተገኙ ክሬዲቶች ሪፖርት ነው።

G. የአጠቃላይ ድምር ውጤት ነጥቦች በመደበኛ ኮርሶች እና የላቀ ደረጃ ኮርሶች እንዲሁም ሁሉንም የላቀ ደረጃ የተሰየሙ ኮርሶች ካልሆነ በስተቀር ከክፍል ውጤት ነጥቦች ጋር ተመሳሳይ ናቸው። በሚከተለው ሚዛን መሰረት የአጠቃላይ ውጤት ነጥብ ማለት ክሬዲት-በሚያስገኙ ኮርሶች የተማሪው(ዋ) አሃዛዊ ውጤት ነው፡

| ክፍል | የክፍል ውጤት ነጥቦች<br>መደበኛ | የላቀ/ከፍተኛ ደረጃ |
|---|---|---|
| A | 4 | 5 |
| B | 3 | 4 |
| C | 2 | 3 |
| D | 1 | 1 |
| E | 0 | 0 |

H. የአጠቃላይ ድምር ውጤት አማካይ ነጥብ (WGPA)፣ የክፍል ውጤት አማካይ ነጥብ (GPA) ለመደበኛ የክፍል ውጤት ከአጠቃላይ ተተኪ ከፍተኛ ደረጃ ኮርሶች የተገኙ ነጥቦችን በመተካት ዳግመኛ የተደረገ ስሌት ነው። WGPA የሚሰላው በጠቅላላ የተገኙት የውጤት ነጥቦችን በስሌት ውስጥ ለተካተቱ ለጠቅላላ የኮርስ ክሬዲቶች ተካፍለው ነው። WGPA ሦስተኛው የዴስማል ነጥብ ቦታ ከአራት የሚበልጥ ከሆነ፣ ወደ ሁለት ነጥብ ቦታ በማጠጋጋት በሁለት አሃዞች ይጻፋል።

III. **ቅደም-ተከተሎች**

A. GPA እና WGPA ስሌት

1. በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እያሉ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶች በማጠናቀቅ ክሬዲት ለማግኘት፣ የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች ልክ እንደሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ተፈላጊ የማጠቃለያ ውጤቶችን A፣ B፣ C፣ ወይም D ማሟላት ይኖርባቸዋል።

a) ከ 2016–2017 የትምህርት ዓመት በፊት 6ኛ ክፍል ለገቡ ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ እያሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኮርሶችን የማጠናቀቂያ ውጤት እና ክሬዲት በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቁት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትራንስክሪፕታቸው ላይ ሪፖርት የሚደረግ ሲሆን በተማሪ አጠቃላይ ድምር ውጤት GPA/WGPA ስሌት ውስጥ ተካትቷል።

b) በ 2016–2017 የትምህርት ዓመት ወይም ከዚያ በኋላ 6ኛ ክፍል ለገቡ ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ እያሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኮርሶችን ያጠናቀቁበት ውጤት እና ክሬዲት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትራንስክሪፕታቸው ላይ ሪፖርት ይደረጋል። ነገር ግን የተገኘው ውጤት የተማሪን አጠቃላይ ድምር ውጤት ካላሻሻለ በስተቀር በተማሪ GPA/WGPA ስሌት ውስጥ አይገባም። በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እያሉ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚሰጠው ኮርስ የተማሪን አጠቃላይ

GPA/WGPA ካሻሻለ፣ MCPS በቀጥታ ይተገብራል።ወላጆች/አሳዳጊዎች በቀጥታ ስሌት ውስጥ እንዳይገባ ከፈለጉ የትምህርት ቤቱን ካውንስለር ማነጋገር ይችላሉ።

2. በተራዘሙ-ቀናት እና በተራዘመ-ዓመት በሚወሰዱ ፕሮግራሞች የሚሰጡ ኮርሶች ሌሎች መስፈርቶችን በሚያሟሉበት ጊዜ በስሌቶቹ ውስጥ ይካተታሉ።

3. ከ MCPS ውጪ በሆኑ ተቋማት የሚሰጡ የጸደቁ ኮርሶች (በመማሪያ ክፍል፣ የተልእኮ ትምህርት ወይም ኦንላይን ኮርሶች) በሥራ ላይ የተወሰደ ጥናት፣እና በዝውውር ለተላለፉ ኮርሶች የተሰጡ ክሬዲቶች፤ ለመመረቂያ ክሬዲት ተይዞላቸው ከሆነ፣ በ GPA/WGPA ስሌት ውስጥ ይካተታሉ። እነዚህ ኮርሶች ወደ ተማሪው(ዋ) ማእከላዊ የመረጃ ቋት በተለይ መመዝገብ አለባቸው። (MCPS Regulation ISB-RA ይመልከቱ፣ ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለመመረቅ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች።)

4. የተተዉ ኮርሶች ውጤቶች እና ክሬዲቶች ለአማካይ የክፍል ውጤት GPA እና ለአጠቃላይ ውጤት አማካይ WGPA ስሌት እንደሚከተለው ይመዘገባሉ፡-

   a) ተማሪ የተዋቸው ኮርሶች።

      (1) አንድ ተማሪ ክፍል በጀመረ(ች)በት ሴሚስተር 25ኛው የትምህርት ቀን ላይ ወይም ከዚያ በፊት ኮርሱን ካቋረጠ(ች)፣ በተማሪው(ዋ) ቋሚ መዝገብ፣ ትራንስክሪፕት እና በሪፖርት ካርድ ላይ ምንም ውጤት አይመዘገብም።

      (2) ተማሪው(ዋ) የሴሚስተሩ ትምህርት ከተጀመረ 25ኛው የትምህርት ቀን በኋላ ካቋረጠ/ች “W,” ወይም “Withdrew” ፣ ያቋረጠ(ች)በት ቀን፣ እና ባቋረጠ(ች)በት ቀን የነበረው/የነበራት አማካይ ውጤት በቋሚ የተማሪ ሪኮርድ፣ ትራንስክሪፕት እና ሪፖርት ካርድ ላይ ይመዘገባል።

   b) ተማሪው(ዋ) ሴሚስተሩ ከተጀመረ 25ቀን በኋላ በቅድመ ይሁንታ ከላቀ ደረጃ ወይም ከከፍተኛ ችሎታ ኮርስ በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ (የኮርስ-ደረጃ ለውጥ) መሸጋገር ካለበ(ባ)ት በተማሪው(ዋ) ቋሚ ትራንስክሪፕት ላይ ምንም ልዩ ማስታወሻ ሳይመዘገብ በተሳካ ሁኔታ ለተጠናቀቁት ኮርሶች ተገቢው ክሬዲት ይሰጣል። "The Office of Curriculum and Instructional Programs" የሥርዓተ ትምህርት እና የትምህርት ፕሮግራሞች ጽህፈት ቤት አንዳንድ የተፈቀደ ደረጃ ላይ ያሉ ኮርሶችን ማዛወር ሊያጸድቅ ይችላል፣ እነዚህም በአፈጻጸም መመሪያ ውስጥ የተገለጹ ሲሆን ከትምህርት ቤት ካውንስለሮች ማግኘት ይቻላል።

5 ማንኛውም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቀ(ች) ተማሪ MCPS Regulation IKA-RA ስለ ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግ ላይ እንደተገለጸው ውጤት ለማሻሻል ትምህርቱን እንደገና መውሰድ ይችላል/ትችላለች።

6 ከሌላ የትምህርት ተቋም ወይም ት/ቤት የተዛወሩ ክሬዲቶች እና ውጤቶች በርእሰ መምህር/ተወካይ አማካይነት ወደ MCPS የክሬዲት ሥርዓት ተቀይሮ ስሌት ዉስጥ ይካተታል።

   a) በተለምዶ MCPS ውስጥ የማይሰጡ የትምህርት ዓይነቶች ለምሳሌ፡- የኃይማኖት ትምህርት ወይም የአሽከርካሪነት ትምህርት የመሣሰሉ ኮርሶች ከ MCPS የኮርስ አላማዎች ጋር የሚሳለጡ ካልሆነ በስተቀር አይካተቱም።

b) በ MCPS ያልተማሩት የላቀ-ደረጃ ኮርስ ነገር ግን በ MCPS ከሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች ጋር ተመጣጣኝነት ካላቸው ይካተታሉ።

c) ከሌላ ተቋም የተላለፉ (የ MCPS ያልሆኑ ኮርሶች) በዚህ ዓይነት የተጻፉ ክሬዲቶች "O" (Outstanding)፣ "S" (Satisfactory) እና "U" (Unsatisfactory) ወይም በአሃዝ ወይም በመቶኛ/በፐርሰንት የተጻፉ ውጤቶችን ት/ቤቱ ወደ A፣ B፣ C፣ D፣ እና E መመዘኛዎች መተርጎም አለበት። እነዚህ ኮርሶች በኮምፒውተር የተማሪ መረጃ ቋት ውስጥ ለብቻ መመዝገብ አለባቸው።

B የተማሪ ትራንስክሪፕቶች

1. ትራንስክሪፕቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ።

a) ሴሚስተሩ ከተጀመረ ከ 25ኛው የትምህርት ቀን በኋላ የተጠናቀቀ ወይም የተቋረጠ ማንኛውም የ MCPS ኮርስ፣ ኮርሱ የተተወበት ቀን እና በለቀቀ(ች)በት ጊዜ የነበረውን ውጤት የሚያሳይ።

b) እንደገና የተወሰደ እና የተጠናቀቀ ኮርስ ከፍተኛው ነጥብ እና ክሬዲት ብቻ።

c) MCPS ደንብ ISB-RA ድንጋጌ መሠረት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ መስፈርቶች ላይ እንደተገለፀው በተራዘመ ቀናት ወይም በተራዘመ ክፍለ-ጊዜ ወይም ከ MCPS ሌላ ተቋም አማካይነት የተሰጠ ማንኛውም የተጠናቀቀ ኮርስ።

d) የከፍተኛ ችሎታ (ልቀት) ስያሜ፣ የ MCPS የብቃት ሰርተፍኬት እና ከፍተኛ ደረጃ ኮርሶች።

e) በእያንዳንዱ ኮርስ የተገኙ ውጤቶች እና ክሬዲቶች።

f) ድምር የክፍል ውጤት አማካኝ እና የአጠቃላይ ውጤት ነጥብ አማካይ።

g) የምረቃ ቀን

2. ርእሰመምህር/ተወካይ የሚከተለው ኃላፊነት አለባቸው።

a) የእያንዳንዱ ተማሪ ውጤቶች እና የተማሪን ሪከርድ በትክክል እንደሚያንጸባርቁ ማረጋገጥ፣ በተራዘሙ ቀናት ወይም በተራዘመ-ዓመት ክፍለ ጊዜ የሚሰጡ ኮርሶች፣ (የክፍል፣ የተልእኮ ትምህርት ወይም የኦንላይን ኮርሶች) ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውጪ ባሉ ተቋማት የጸደቁ ኮርሶችን ጨምሮ) ፣ የዝውውር ኮርሶች እና በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያሉ በተሳካ ሁኔታ የተጠናቀቁ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኮርሶች።

b) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እና ድህረ ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ተቋማትን ጨምሮ ተማሪው(ዋ) መመዝገብ ወደሚፈልግባቸው ትምህርት ቤቶች ትራንስክሪፕት መስጠት።

c) ይህ መረጃ እንዲሰጥ በተማሪው(ዋ) ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም ብቁ በሆነ(ች) ተማሪ የተፈቀደ እስከሆነ ድረስ ለስኮላርሺፕ ፋውንዴሽን፣ ለቴክኒክ ተቋማት እና ለአሁን ወይም የወደፊት ሥራ ቀጣሪዎች ትራንስክሪፕት መስጠት።

3. የዋና ስትራቴጂክ ኢንሼቲቭስ ጽ/ቤት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትራንስክሪፕት ላይ GPA እና WGPA መመዝገቡን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት።

4. ትራንስክሪፕት እና ሌሎችም የተማሪ ሪኮርድ መረጃዎችን ለማግኘት የሚቻለው በ MCPS Regulation JOA-RA ድንጋጌ መሠረት ይሆናልየተማሪ መረጃዎች/ሪከርድስ።

5. በቦርድ ፖሊሲ JNA መሠረት ት/ቤቶች የተማሪን ትራንስክሪፕት እስከ ሦስት ጊዜ ያለምንም ክፍያ ይሰጣሉ ስለ ተማሪዎች የሥርዓተ ትምህርት ወጪዎች።

**የዚህ ደንብ ታሪክ፦** የቀድሞ ደንብ ቁጥር 340-3፥ ኦገስት 20, 1980፣ ተሻሽሏል ፌብሩዋሪ 1986፣ ተሻሽሏል ዲሴምበር1986፣ ተሻሽሏል ጁን 10, 1988፣ ተሻሽሏል ጁን 24, 1993፣ ተሻሽሏል ሜይ 23, 2000፣ የጽ/ቤቱ መጠሪያ ተሻሽሏል ጁን 1, 2000፣ ተሻሽሏል ሜይ 20, 2008፣ ተሻሽሏል ሜይ 12, 2010፣ ተሻሽሏል ኦገስት 22, 2013፣ ተሻሽሏል ጁን 27, 2016፣ ተሻሽሏል ጃኑዋሪ 30, 2018፣ ተሻሽሏል ኤፕሪል 27, 2022፣ revised ፌብሩዋሪ 3, 2023።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* | MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| "Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org | |

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ጁን 2022